# <u>አዲስ አመት ለኛ ይሁን</u>

ከቀመሩ ደሳለኝ

አዲስ ዓመት ይሁን ለኛ ለሁላችን
ጥሩ የደስታ፡ የሰላም ዘመን
መልካም አውደ ዓመት ለኢትዮጵያ አገራችን

እንኳን አደረሰን  ለሁለት ሺ አምስት
አሮጌውን ጨርሰን አለፈ ያ ወራት
ክፍ መከራውን ሁሉን ያዬንበት
መጥፎን አሳልፎ አዲሱ መጣልን
ያ አመት ተጨርሶ ሌላ ተተካልን
ይመስገን ፈጣሪ ለዚህ አበቃን።

ያምናው ቀን አለፈ ጊዜው ተቀየረ
አቻምናም አለፈ አምናም ተባረረ
አምላክ አይዘነጋ ዝም ብሎም አልቀረ
አማኙን የሚወድ ኢትዮጵያን ተቼረ።

አዲስ ዓመት መጣ አለፈ ያምናው
ሌላ ዘመን ሆነ ሄዴ የነበረው
እንዲታወስ ሆኖ ያ ክፉ ሥራው
ያልተደሰትንበት መጥፎ ጨፍጋጋው
ታሪክ ይመዝግበው ዘመን ይውቀሰው
ዘመናት ይፍረደው ጊዜ ያስታውሰው።

አምና ዛሬ አይደለ ይህ ዓመት የደስታ
ትናንት አለፈና ተስፋ አየን በርጋታ
ብዙም ሳይራራቅ በአንድ ሰሞ እርምታ
አሳስቦ ጠራ ያን የዘር በሽታ
ነቃቅሎ ሊያጠፋው ሁሉንም በተርታ።

አዲስ ዓመት ሲለወ በጥሩ ዋዜማ
እያጉረመረመ ሙብርቅ እያሰማ
ዝናብ ውሽንፍሩ ሆኖ ቀዝቃዛማ
ለአገር ለወገን በጣም በሚስማማ
ትቢያው ተጠራርጎ ሊያሳምር ቦታውን
ሕዝብ በተስፋ አምሮበት ሊቀበል ዘመንን
አዲስ ዓመት መጣ ይዞ ነጋሪቱን።

ያለፈን ሸኝቶ የጠላውን ዓመት
በዋዜማው ጸዳ አማረ የናት ቤት
የውድ አገራችን ኢትዮጵያ የኛ እናት

መስከረም ሲጠባ አደይ ሲፈነዳ
አዲስ ዓመት ይዞ ወጋገን ማለዳ
ወገን እንዲደሰት እንዲያምር ሊጸዳ
አበቦች ፈንድተው በመልካም ቀለማት
አየን በወጋገን የኢትዮጵያን ውበት
ለሕዝብ ደስታ ብርሃን ለነፃነት።

ሆያ ሆዬ ብለህ አቃጥል ችቦህን
ቆመህ አቀጣጥል በአራቱም ማዕዘን
ይጭስ ይንደድ ይለቅ ጭራሮ ማሰሪያው
አመድ ሆኖ ይክሰም ይቆስቆስ ችቦው
በኖ ታጥቦ ይጥፉ ሁሉም ቆሻሻው።

ይህ ዓመት ይመስገን እንዘከረው
ከዓመት ወደ ዓመት ይከበር ደስታው
ፈጣሪ ይመስገን ለዚህ አደረሰን
ያን ዓመት አሳልፎ ለዚህ ቀን አበቃን
ሁሉን የፈጠረ ሁሉን በማድረጉ
አምላክ ክብሩ ይስፋ ይመስገን በእጅጉ።

ዛሬስ ምስጋና ነው ልመና ልቀንስ
ፈጣሪ አሳካልን ሁሉንም ቀስበቀስ
መጭው ዓመት የኛ ፈጣሪ ባቀደው
ሕዝብ ይህን ያመስግን ፈቃዱን ይባርከው
በእውነት በቅንነት ፈጣሪን አምልከው

ኃያሉ አምላካችን ታምር አሳይቷል
በኢትዮጵያ አገር ላይ ባውዛውን አብርቷል
ይህ ዓመት እንድሆን ፋኖ የነፃነትህ
በፅናት በአንድነት ቁም ለደህንነትህ
በቃል ኪዳን ጠንክር ለውድ አገርህ
ኩራ በታሪክህ ትውልድ እንዲያከብርህ

**ዓመቱ ይባረክ ያፅናን በተግባር !**

መስከረም 1/2005